# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 52

የካቲት 5 ቀን 2015 ዓም (12-02-2023)

ካለፈው ሳምንት እሁድ ምሽት ጀምሮ ያገራችንን ሁኔታ ስንዳስስ የሥርዓቱ እብሪትና የሕዝቡም አልበገሬነት እያደገ መሄዱን እንገነዘባለን።የሲኖዶሱን ውሳኔ ተከትሎ ከሰኞ ጀምሮ ለሦስት ቀናት ጥቁር በመልበስ የማህሌትና የጾም አዋጅ በታወጀው መሠረት ምእመናኑ ከእሁድ ማታ ጀምሮ በዬቤተክርስቲያኑ በመሰባሰብ በተለይም የሕገወጡ የነአቶ አካለወልድ ወይም ሳሪዎስ ቡድን በአብይ አህመድ ትእዛዝ በወታደር ታጅቦ ቤተክርስቲያናትን እዬሰበረ መግባት በመጀመሩ ሌሊቱን በደጀሰላም ግቢ ጥበቃ ሲያደርግ አድሯል።

ሕገወጡ ቡድን በወለጋና በጅማ የጀመረውን የመንበር ሰበራ አጠናክሮ በሻሼመኒ ባደረገው ወረራ ከምእመናኑ በኩል የገጠመውን ተቃውሞ በጥይት ተኩስ ለመበተንና መንበሩን ለመቆጣጠር የቻለ ሲሆን የ37 ምእመናን በተለይም ወጣቶችን ሕይወት ቀጥፏል፣በብዙ መቶ የሚቆጠሩም የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል።ቁጥራቸው በቅጡ ያልታወቁ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆችም ታፍሰው ወደ አልታወቀ ቦታ ተወስደዋል።ይሙቱ ይኑሩ አልታወቀም።በዚህ የተደፋፈረው ወንጀለኛ ቡድን ፊቱን ወደ ወሎ ኮምቦልቻና ከሚሴ አዙሮ በኮምቦልቻ በሕዝቡ ተቃውሞ ያሰበው ሳይሳካለት ከአውሮፕላን ጣቢያ ሳይወጣ በመንግሥት ሔሊኮፕተር ወደ መጣበት ተመልሶ ሄዷል።ሕዝባዊ ተቃውሞው በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ እዬተቀጣጠለ በመሄዱ ለመንግሥትና ለአማጽያኑ የማያዳፍኑት ሰደድ እሳት ሆኖባቸዋል።በአንዱ በኩል ሊያጠፉት ሲሞክሩ በሌላው በኩል እዬተለኮሰ ግራ አጋብቷቸው ሰንብቷል።አብይ አህመድ አገር በዚህ ቀውጢ ስትናጥ ምንም እንዳላየና እንዳልሰማ ባለሟሎቹን አስከትሎ ወደ ጣልያን አገር ሄዷል። ሆኖም ግን ከአገር ቤት የሸሸው ተቃውሞና ውግዘት ተከትሎት ጣልያን ጠብቆታል።በጣልያን የሚኖሩ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞችና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጨፍጫፊና ገዳይ!፣ለፍርድ መቅረብ ያለበት ወንጀለኛ! እያሉ ስሙን እዬጠሩ በማጋለጥ አሸማቀውታል። ወደ ጣልያን የሄደበትን ጉዳይ ስናሰላው ከዚህ ቀደም ሲል ለጥይት ማምረቻ የገዛው መሳሪያ(ማሽን) በተጭበረበረ ሰነድ ሊወጣ ሲል የጣልያን የቁጥጥር መስሪያቤት በማገዱ ያንን ለማስለቀቅና ተጨማሪ የጦር መሣሪያ ለመግዛት እንዲሁም ብድር ለመጠዬቅ እንደሆነ ለማወቅ ችለናል። በሮም ቆይታው ከካቶሊኩ ጳጳስ ጋር ተገናኝቷል፤የመታሰቢያ ስጦታም ተለዋውጧል። በቫቲካን የሄደበት ምክንያት በዝርዝር ባይገለጽም በእኛ እምነት ዕቃ ለመለዋወጥ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ በኩል የገጠመውን ተቃውሞ ለማብረድ ጣልቃ እንድትገባ ለመጠዬቅ መሆኑ ጉብኝቱን ተከትሎ ከካቶሊክስ ቤተክርስቲያን በኩል የተላከው የድጋፍ መግለጫ በይዘቱ መልካም ቢሆንም ከዚያም በላይ መልእክት ያለው ሳይሆን እንዳልቀረ አመላካች ነው።ከሮም ጉብኝቱ ቀጥሎ ለተመሳሳይ ጥያቄ ወደ ትንሿ ያውሮፓ አገር ማልታና ኋደኛዬ ብሎ ወደሚጠራው ማክሮን አገር ፈረንሳይ ተጉዞ በሶስተኛ ቀኑ ተመልሷል።በሁለቱም አገሮች ጉብኝቱ ምን አድርጎ እንደመጣ የተሰጠ መግለጫ የለም፤የሚጠይቅም ሕዝብም ድርጅትም የለም።እንደልማዱ ሲወጣና ሲገባ ወጣ ገባ እያለ የሚያይና የሚያወራ ነው።ይህም ጠያቂ የለብኝም ለሚል እብሪት ዳርጎታል።

ጉዞውን በተመለከተ ብዙዎች አገር ውስጥ ዜጎቹ ሲጨፈጨፉ ለይምሰል እንኳን ቢሆን ሃዘኑን ሳይገልጽ መሄዱንና ከተመለሰም በኋላ በቱርክ በደረሰው የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ለሞቱት የሃዘን መልእክት መላኩን ለራሱ ሕዝብ ደንታ የሌለው አስመሳይ ነው ሲሉ ተችተውታል።እኛ ግን እራሱ ላስጨፈጨፈው የሃዘን መግለጫ ያውጣ ማለት አንዱን ገዳይ ወንጀለኛ ለምን ለቅሶ አልደረሰኝም ብሎ

መጠዬቅ ይሆናል፤ገዳይ በካቴና ታስሮ ለፍርድ ይቅረብልኝ ይባላል እንጂ እንደተነጂ ቤተሰብ ሃዘን ላይ ይቀመጥ አይባልም።እንዲህ ነው ጠላትና ወዳጅን ያለማወቅ አባዜ!

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች እንደ አንድ ሰው መካሪ፣እንድ አንድ ሰው ተናጋሪ ሆነው በያገሩ በሥርዓቱና በሕገወጡ ቡድን ላይ ያላቸውን ጥላቻና ተቃውሞ መግለጻቸውን ሳያቆሙ በመቀባበል በተለይም በአገር ውስጥ የሕጋዊ ሲኖዶሱን የመጨረሻ ትእዛዝ በመጠባበቅ ብዙ ቀናት አሳልፈዋል፤ በዬቀኑም በአብይ አህመድ መንግሥት በሚታዘዝ ወታደርና የሕገወጡ የሳሪዎስ መንጋ ሞትና መቁሰል፣ መታሰርና መንገላታት ደርሶበታል፤እዬደረሰበትም ነው።የሕጋዊውን ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስን አቋም በመደገፍ ወያኔም በሚቆጣጠራት ትግራይ በተለይም በአክሱም ከተማ አንድ ሲኖዶስ፣አንድ ተዋህዶ ቤተክርስያን፤አንድ ፓትሪያርክ የሚለው የአብሮነት ድምጽ ሲያስተጋባ ሰንብቷል።የአቡነ ማትያስ ፊርማ ያረበበት ደብዳቤ ለትግራይ አገረ ስብከት የተላከ መሆኑን ብንሰማም ከትግራይ በኩል የተሰጠ ግልጽ ምላሽ መኖሩን የሚያረጋግጥልን ግን አላገኘንም።ሆኖም ግን የትግራይ እናቶች ያሳዩት ጸሎትና ሃዘን በራሱ ለኦርቶዶክስ አማንያን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ አገራቸው እጣፈንታ ለሚያሳስባቸውና ለሚያስጨንቃቸው ዜጎች የአንድነት ማሳያ ምልክት ነው በሚል ደስታ ተስፋቸውን አደንድኖታል። ከቀናት በኋላ ደግሞ ይህንን የሚቃረን ማለትም የትግራይ መነኮሳትና ሃገረ ስብከቱ ልዩነታቸውን ገለጹ የሚል ወሬ ተሰራጭቷል።ውሸት ከላይ እስከታች በሰፈነበት አገር ትክክለኛውን ለማወቅ ያዳግታል።የትግራይ ሕዝብ ከእምነቱ አንጻር ሲታይ ለአብይ አህመድ ሴራ እምነቱን አሳልፎ ይሰጣል አንልም። ሆነም ቀረ ወደፊት የምናዬው ይሆናል።

ሰኞ ጥር 29 ቀን 2015 ዓም ከፍርድ ቤት ይጠበቅ የነበረው የቤተክርስቲያኗ የአቤቱታ ውሳኔ መቋጫ ሳይገኝለት ለእሮብ ለዬካቲት 1 ቀን 2015 ዓም ቀጠሮ ተሰጥቶ እንደተላለፈ በእለቱ በጠበቆቹ በኩል ማብራሪያ ተሰጥቶ ነበር።ቀጠሮውን ተከትሎ እሮብ እለት ፍርድ ቤት የዋለው ችሎት በአንድ ባልተወከለ ግን ልወከል እችላለሁና ቀጠሮ ይተላለፍልኝ ብሎ በመጠዬቁ ሌላ ቀጠሮ ለጥቅምት 3 ቀን 2015 ዓም ሰጥቶ ብይን ሳይሰጥ ተነስቷል።የሚገርመው ነገር የፍርድ ሂደቱን ያሰናከለው ያልተወከለና የውክልና ማስረጃ ያላቀረበ ግለሰብ መሆኑ ብቻም ሳይሆን ከሕገወጡ ቡድን ጋር ክስ የቀረበበት ወንጀለኛ መሆኑ ነው። ይህ ተከሳሽ የችሎት ስርዓቱን ለማስቀልበስ መቻሉ ምን ያህል የመንግሥት ጨዋታ እንዳለበት በግልጽ ያሳያል።የሕጋዊ ሲኖዶሱም ጠበቆች ተከሳሽ ጥብቅና ሊቆም አይችልም ብለው ለመቃወም አለመሞከራቸው በቀጣይ ለሚሰሩት ሥራ ብቃታቸውን ከጥያቄ ውስጥ ያስገባ ነበር።

የሲኖዶሱን ትእዛዝ ተከትሎ ከሰኞ እለት ጀምሮ ሕዝቡ ጥቁር ልብስ ለብሶ ወደ ቤተክርስቲያንና ወደ መሥሪያ ቤት ሲሄድ በሥርዓቱ የጸጥታና የኦነግ ታጣቂ ጠብደሎች እዬታገደና እዬተደበደበ ወደ እስር ቤት ሲነዳ በምስል ታይቷል።የመሥሪያ ቤት ሠራተኞችም ጥቁር ለብሳችሁ አትገቡም ተብለው ከሥራቸው ታግደዋል ። ልብሳችሁን ቀይሩ ቢባሉ እምቢኝ!ሥራዬ ከሃይማኖቴ አይበልጥብኝም በማለት በዚህ አስከፊና ችግር በተመላበት፣ኑሮ አዳጋች በሆነበት ወቅት የመጣው ይምጣ ብለው እራሳቸውን ከሥራቸው ያሰገዱ ጥቂቶች አይደሉም።እንዲህ ነው የዓላማ ጽናት ማለት!እነዚህ ቆራጦች እንደሌላው እጃቸውን ጠብቆ የሚያድር ቤተሰብ ሊኖራቸው ይችላል፤ግን ጥያቄው የመኖርና ያለመኖር፤የነጻነትና የመብት ከዚያም በላይ ያገር ጉዳይ ስለሆነ የመረጡትን መርጠዋል።ምርጫቸው ግን የሚያፍሩበትና አንገታቸውን የሚደፉበት አይደለም።ቤተሰባቸውም ምንም እንኳን ለችግር ቢጋለጥም ክፉ ቀን ሲያልፍ የሚኮራበት የጀግንነት እርምጃ ነው።እንደነዚህ አይነቶቹ አገር ወዳዶች ባሉበት አገር ደግሞ ለሆዱ የሚያድር፤ ለወገኑ የማያዝንና ለአገሩ የማይቀረቀር መኖሩ ሲታይ ጉድ!አጃኢብ! ያሰኛል።

አሁን ላይ በአነጋውያኑ ተብዬው ቡድን በሚመራው ሥርዓት ላይ ያልተነሳ የህብረተሰብ ክፍል የለም። የኪነት ባለሙያው፤የባንክ ሠራተኛው፣መምሕሩ፣ሃኪሙ፤ተማሪው እምቢተኝነቱን በቃላት ብቻ ሳይሆን በተግባርም ገልጿል።የቤተክህነትን አዋጅ ተቀብሎ ታማኝነቱንና አብሮነቱን ገልጿል፥በመግለጽም ላይ ነው።ሌላው ቀርቶ የአዲስ ቴሌቪዥን ዜና አቅራቢ የሆነው ሳህለገብርኤል ይትባረክ የተባለው ጋዜጠኛ ጥቁር ልብስ ለብሶ ዜና በማንበብ ላይ እንዳለ ፕሮግራሙን አቋርጦ እንዲወጣ ተደርጓል።እሱም ልብሱን ቀይሮ ለመቀጠል ባለመፍቀዱ ሥራውን ከነጭራሹ ለቆላቸዋል። በአሁኑ ጊዜ ጥቁር መልበስና በአንገት ላይ መስቀልና ማተብ ማሰር የሚያሳስርና የሚያስደበድብ ወንጀል ሆኗል።የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉዳይ(ኢሰመጉ) ተቋምም ሰዎች በምነታቸው ምክንያት እንግልትና ጉዳት እዬደረሰባቸው ነው፤ ሞት ድብደባ፣ እንግልትና እስራት ደርሶባቸዋል።የማመን መብት ተጥሷል።ጉዳዩን ለዓለም አቀፍ ተቋማት ገልጨ እርምጃ እንዲወስዱ እጠይቃለሁ ብሏል።

ተቃውሞው በሕዝቡ በኩል ብቻም ሳይሆን የአብይን መንግሥትም እዬቦረቦረው መጥቷል፤የአራት ኪሎ መንግሥት በቋፍ ላይ ነች።ጥቂት ባለሥልጣኖችም እምነቴ ከሥልጣኔ አይበልጥም፣ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጋር እቆማለሁ በማለት እራሳቸውን ከሥልጣን ማሶገዳቸው ተሰምቷል።የኦርቶዶክስ ተከታይም ብቻ ሳይሆኑ የፕሮቴስታንትና የእስልምና እምነት ተከታዮችም ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጋር መቆማቸውን ገልጸዋል።

ማክሰኞ እለት በአዲስ አበባ በሸሮሜዳ ወጣቱ አደባባይ ወጥቶ እዬዘመረ ተቃውሞውን ሲገልጽ፣ ከጸጥታ ሃይሎችም ጋር ሲተናነቅ ውሏል።የጉዳቱ መጠን አልታወቀም እንጂ ብዙዎች መቁሰላቸው ተሰምቷል።ብዙ ወጣቶችም ታፍሰው ወዳልታወቀ ቦታ ተወስደዋል፤ይሙቱ ይኑሩ አልታወቀም።

በሻሼመኒ ቤተሰብ የሞቱትን እንዳይቀብርር አስከሬን ተከልክሏል።የቆሰሉትንም ሆስፒታል ሄዶ እንዳይጠይቅ በመንግሥት ተከልክሏል።የከፋ፣ማጅና ቤንጂ አገረ ስብከት ጳጳስ አቡነ እስቅኤል ከሕዝቡ ጋር ሳይገናኙ በጅማ አውሮፕላን ማረፊያ ታግደው ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ ተደርገዋል።

መንግሥት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሲኖዶስ ተከታዮች ለእሁድ የካቲት 5 ቀን 2015 ዓም ሊያደርጉ ያሰቡትን አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ ለማደናቀፍ የግማሽ ማራቶን እሩጫ እንዲዘጋጅ የሚመለከተውን ክፍል ማዘዙ ቢሰማም ይፋ አልሆነም።የወንበዴው የአቶ አካለወልድ ወይም ሳሪዎስ ቡድንም በዚሁ እሁድ ቀን የድጋፍ ሰልፍ ጠርቷል።ይህ በመንግሥት በኩል ግርግርና ግጭት እንዲቀሰቀስ ሆን ተብሎ የተሸረበ ሴራ ለመሆኑ አያጠራጥርም።በዚህ መካከል አብይ አህመድ ሊጫወት ያሰበው ቁማር ለሰላም ሲባል ሰልፎቹ ተከልክለዋል የሚል ትእዛዝ የሚያስተላልፍ ይሆናል የሚለው ግምት በተግባር ተተርጉሞ ከአፍሪካ ህብረት ጉባኤ ጋር የተያያዘ የጸጥታ ጉዳይ በማስመሰል የጊዜያዊ እገዳ እስከ እሁድ የካቲት 5 ድረስ ጥሏል።ከዚያም አልፎ ተርፎ መንግሥት ለመጣል የታሰበ መፈንቅለ መንግሥት ነው የሚል ሽፋን ሰጥቶታል።በቀጣይ ቀናት የሚቃወሙትን የፖለቲካ ሰዎች እያፈሰ ከማሰር እንደማይመለስ በጋዜጠኛና በባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ አመራር በሆነው በስንታዬሁ ቸኮል ላይ ጀምሮታል።ቀደም ሲልም አስሮ የሚያሰቃዬው አዛውንቱ ታዲዎስ ታንቱ እስከ አሁን ድረስ ካለፍርድ እዬማቀቀ ነው።

ስንታዬሁ ቸኮል በነጋ በጠባ እንደ ጠፍ ላም እዬታገተ በእስር ቤት ሲማቅቅ ይህ የመጀመሪያው አይደለም።ለተመልካች ልብ በሚሰብር መልኩ በልጆቹ ፊት ከቤቱ በካቴና ታስሮ መወሰዱ ግን የሥርዓቱን የጭካኔ ደረጃ ያሳዬ ድርጊት ነው።ስንታዬሁ ጥቁር በመልበሱ እንጂ ሌላ የሠራው ወንጀል የለም።እሱም በሃይማኖቴ ላይ አል,ራደም የፈለገው ይምጣ በማለት ቤተሰቡንም ለማጽናናት ሞክሯል።

አብይ አህመድ በዚህም ብቻ አልቆመም ፣ነገራት እዬተካረሩ እንዲሄዱ ተግቶ በመሥራት ላይ ነው። የአቶ ሳውሪዎስ ቡድን ገዳማትና ደበራትን በጉልበት እዬሰበረ፣ምዕመናኑን እያሸበረ ሲሄድ እዬደገፈ ከመሄድ አልተቆጠበም።የአገር የማፈራረሱ እቅድ እንዲሳካ በሽዎች የሚቆጠር የኦሮሙማ የታጠቀ ሃይል አዲስ አበባ ድረስ ጭኖ አስገብቷል። በወታደራዊ እንቅስቃሴ የአዲስ አበባ ከተማ የኡክሬኗን የኪዬቭ ከተማ የምትወዳደር መስላለች።

ባንኩንም ታንኩንም የያዘው የኦሮሙማ ቡድን በሚቆጣጠረው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም በኩል በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ ጦርነት ከፍቷል።የኦነጉ አባል የባንኩ ዋና ሥራአስኪያጅ ለዬቅርንጫፍ የባንኩ አስተዳዳሪዎች ባስተላለፈው ትዕዛዝ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ያላትን የገንዘብ መጠን ዝርዝር በአስቸኳይ እንዲልኩለት አዟል።ለዘረፋ መሆኑ ግልጽ ነው።አንድ ደንበኛ በወንጀል የገንዘብ ሽክርክሪት ውስጥ መግባቱ ካልተረጋገጠና ፍርድ ቤትም ካልወሰነ ይህንን አይነት እርምጃ ሊወሰድበት አይችልም።በባንክ አሠራር የደንበኞች ሙብትና ምስጢር የተጠበቀ ነው። በኦነጎች ዓለም ግን የማይጣስ ሕግ የለም።ለሕግ ባዳና እንግዳ በመሆናቸው የሚገርም አይሆንም።ዱሮስ ቢሆን ከአውሬ ምን ይጠበቃል?

በጣም ልብ የሚሰብረው ሌላው አሳፋሪ ድርጊት የአብይ አህመድ ቅልብ የኦነግ ፖሊስ በካህናቱ ላይ የፈጸመውን ድፍረት ነው።በምስልና በቃል እንደታዬው ዩኒፎርም የለበሰ አንዱ ወጠምሻ በሰላም ባጠገቡ የቆሙትን ሻሽ የጠመጠሙ ቄስ ተንጠራርቶ በጥፊ ሲለጋ፤በወለጋ የነበሩትን ሌላውን መንኩሴ ሌት ለብርድ ፣ቀን ለሃሩር አጋልጦ በርሃብና በስቃይ ለሶስት ቀናት ከማሰቃዬት በተረፈ ልብሳቸውን አውልቆ ለመግለጽ በማንችለው፣ ለጆሮ የሚቀፍ፣ድርጊት ፈጽሞባቸዋል።ይህ ከፍተኛ ወንጀል የስርዓቱን ምንነት የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ የኦሮሞ ተወላጁን ሁሉ የሚያዋርድና የሚያሳፍር በመሆኑ የኦሮሞ ተወላጅ ወንጀለኛውን ስርዓትና ድርጊቱን የፈጸመውን ቡድን ሊቃጣው ይገባል። በዝምታ ካለፈው ግን ለድርጊቱ ተባባሪ ነው ማለት ነው።

በምእመናኑና በቀሳውስቱ ላይ የሚደርሰው በደልና ግፍ ምህዳሩን አስፍቶ እሮብና ሃሙስ እስከ አርብ ድረስ የዘለቀው የነሳሪዎስ በወታደሮች የታጀበ የቤተክህነት ሰበራ በሰበታ፣በዓለምገና፣በአዬር ጤና ባደረገው ዘመቻ ወለቴ በተባለው ከባቢ በሚገኘው የመድሃኒዓለም ቤተክርስቲያን ደጃ ሰላም በጥይት የተገደሉና የቆሰሉ ብዙ ናቸው።በዬቤተክርስቲያኑ ደጃ ሰላም ምዕመናኑ በተለይም ወጣቱ ቀን ከለሊት አናስደፍርም ብሎ መስዋእትነት ከፍሎ ቤተመቅደሱን ከወራሪዎች ለማዳን ብዙ ተጋድሎ አድርጓል። የሲኖዶሱን ትዕዛዝና ጥሪ በተግባር ገልጿል፣በቀጣይም ለመግለጽ ተዘጋጅቶ የሲኖዶሱን ውሳኔ ሲጠባበቅ ቆይቷል።

ከቤተክህነቱ ወጣ ስንል አቅጣጫም ለማስቀዬር ይሁን አጋጣሚውን ለመጠቀም ከሰሞኑ ከተሰሙት ወሬዎች መካከል የወያኔ መሪዎች የተደረሰበት ስምምነት አልተገበረም የሚል ክስ ይዘው ብቅ ማለታቸው ነው።ሰሞኑን አንድ ላይ መናፈሻ ውስጥ ውስኪ ሲራጩ እንዳልሰነበቱ አሁን ላይ ይህችን ካርታ መምዘዛቸው የሕዝቡ አንድነት ከተጠናከረና የትግራይም ሕዝብ በሃይማኖቱ ሰበብ ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በአንድነት ከቆመ ሊደርስባቸው የሚችለውን አደጋ በመረዳት ያንን ቀልብሶ የተነሱበትን አገር የማፍረስ ዓላማ ከአጋራቸው ከኦነግ ጋር ለማስፈጸም መንደርደሪያ ማድረጋቸው ሊሆን እንደሚችል ስጋታቸውን የሚገልጹት ጥቂቶች አይደሉም፤እኛም ቂጣም ከሆነ ይጠፋል፤ሸልም ከሆነ ይገፋል ወይም ድመት መንኩሳ አመሏን አትረሳ ብለን ስጋታቸውን እንጋራለን።ለጦርነትም ሃይሉን እያሰባሰበና ወደ አማራው ክልል እያስጠጋ መሆኑ ታውቋል።ሕዝብም ሰብስቦ ትግራይን ነጻና ልዑላዊት አገር ሳናደርግ ትግላችን አይቆምም የሚል ቅስቀሳ አድርጓል።ሕዝቡም ለዚያ እንዲዘጋጅ ጥሪ አቅርቧል፤እምቢ ባለውም ላይ እርምጃ እንደሚወስድ አስጠንቅቋል።የአማራው መከራ ገና አላለቀም።

ከሁሉም አቅጣጫ ሰይፍ እዬተሳለበት፣ጠመንጃ እዬተወለወለበት ነው።በዚህ መካከል የሚገጥመውን አደጋ ተረድቶ ለመዘጋጀት አሁንም የመሪ ድርጅት ችግር አለበት።ያ ችግር እስካልተፈታ ድረስ የመጣ የሄደው ሲቀልድበትና ያሻውን ሲያደርግበት ይኖራል፤በመጨረሻውም ታሪኩንም፣ማንነቱንም ከሚያጣበት ደረጃ ላይ ይደርሳል።በስሙ የሚነግዱና ኑሯቸውን የሚያሻሽሉ ግን አልጠፉም።ሥልጣን ላይ ከተቀመጠው ብአዴንና አብን ጀምሮ በመገናኛ ዘርፉም ያሉት ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም።ከነዚህ ሁሉ የጸዳ የፖለቲካና ወታደራዊ ድርጅት አለመኖሩ ለአጭበርባሪዎች ዕድል ሰጥቷል።አሁንም መፍትሔ ካልተገኘና ሃቀኛ መሪ ድርጅት ካልተፈጠረ የአማራው ስቃይና እልቂት ፣የአጭበርባሪዎቹም ተግባር ይቀጥላል።ኢትዮጵያም እንደ አገር የመቀጠሏ ነገር ያበቃላታል።በሰፈር ተሸንሽና ለዘላቂ እልቂትና ግጭት ትጋለጣለች። አሁንም እንደማንኛውም ጊዜ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በተለያዬ ጎራ የተሰለፉት አገር ወዳዶች ልዩነታቸውን ወደጎን አድርገው አገር በማዳኑ ትግል ላይ ተባብረው ለመቆም የሚያስችላቸው የጋራ ግንባር ወይም አመራር ይፍጠሩ እንላለን።ጊዜው እዬሮጠ ነው።ጊዜው የሚድኑበትን የትግል ዋሻ አለያም የሚቀበሩበትን ጉድጓድ የሚቆፍሩበት ይሆናል።መምረጡ የያንዳንዱ አገር ወዳድ አላፊነት ነው።

ወደ ትልቁ ሳምንታዊው እርዕስ ስንመለስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ለጀመረችው የክስ አቤቱታ አርብ በየካቲት 3 ቀን 2015 ዓም መልስ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው ችሎት በሁለት ዳኞች ውሳኔ አስተላልፏል።በተለምዶ በሦስት ዳኞች ችሎት ይሰጥ የነበረ ፍርድ አንዱ/ዷ ዳኛ ባልተገለጸ ምክንያት መቅረቱ/ቷ ለምን የሚል ጥያቄ ቢጭርም ምክንያቱም በተደጋጋሚ አንድ ዳኛ ቢጎል ችሎቱ አልተሟላም በሚል ምክንያት ሌላ ቀጠሮ ይሰጥ እንደነበር ስለሚታወቅ በሁለቱ ዳኞች ብቻ መሰጠቱ ምናልባትም ከነገሩ አሳሳቢነት የተነሳ ሌላ ቀጠሮ ላለመስጠት ታስቦ የተደረገ ነው ብለን ለመቀበል ባንቸገርም፣በሁለትም ዳኞች ቢሆን የተሰጠው ውሳኔ ለሕጋዊ ሲኖዶሱ ጥያቄ በከፊልም ቢሆን መልስ የሰጠ ነው።በከፊል የምንለውም ሌላውን ከፊል ለሕገወጡ እውቅናና መብት የሰጠ መሆኑን በማዬት ነው።የፍርዱ ይዘት ሲጨመቅ ሁለቱም በያዙት ይዞታ ይርጉ የሚል ነው።ያም ማለት ሕገወጡ ሲኖዶስ እዬሰበረ፣እዬገደለ የያዛቸው ቤተክርስቲያኖችን ይዞ ሌላ ሳይሰብር ባለበት ይቁም ማለት ሲሆን ሕጋዊ ሲኖዶሱም ይመለሱልኝ ብሎ የጠዬቀው ጥያቄ የያዝከው ይበቃሃል በሚል መልኩ መመለሱን ታዝበናል።ከዚህ ውጭ ሌላ ውሳኔ የለም፤ቢሸፋፍኑትም አይጠቅምም። ይህም ውሳኔ ቢሆን ለጊዜው እንጂ ዘለቄታነት እንደሌለው ተገልጿል።የዘለቄታው ውሳኔ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚታይ ይሆናል።

የፍርድ ሂደቱን በተከተለና በተናበበ በሚመስል መልኩ የአብይ አህመድ መንግሥት ከዚህ በፊት ልኳቸው ሲኖዶሱ ወግዱ ብሎ የመለሳቸውን ከደጋፊዎቹ የተውጣጣ የሽማግሌ ቡድን መልሶ በመላክ ከሲኖዶሱ ጋር ተስማምተው ለውይይት ወደ ቤተመንግሥት ሄደው የደረሱበትን ውጤት ሲኖዶሱ በዕለቱ ጥሩ ንግግር አድርገናል፣ጥያቄያችን መልስ አግኝቷል የሚል ሽፍንፍን ያለ መግለጫ ሰጥተው ዝርዝሩን በማግስቱ በቅዳሜ የካቲት 4 ቀን 2015 ዓም ይፋ እናደርጋለን ባሉት መሠረት ምንም እንኳን መግለጫው ይሰጣል ተብሎ ከተገለጸበት ሰዓት ከ3 ሰዓት በላይ በመዘግዬቱ በሁሉም ሰው በኩል ስጋት ያሳደረ ቢሆንም ሙሉ መግለጫው ለሕዝቡ ቀርቧል።በዚሁም መግለጫ መንግሥት ጥያቄያችንን ተቀብሎ ለመፈጸም ተስማምቷል።ደስ ብሎናል፣ከአብይ አህመድ ጀምሮ ሁሉም ባለሥልጣናት የችግሩን አይነትና ሊከሰት የሚችለውን ቀውስ ተረድተው ተባብረዋል፤ለዚያም እናመሰግናለን።ከእኛ ጋር የተባበሩትን ሁሉ እናመሰግናለን ።የሞቱትና የቆሰሉት የሰማዕትነት በረከት በማግኘታቸው ደስተኞች ነን ከማለት ባለፈ ተገኘ ያሉትን ውጤት ከመዘርዘር ተቆጥበዋል።

እንደ እውነቱ ከሆነ አብይ አህመድ ሽማግሌዎቹ ላቀረቡለት ጥያቄ በቁጣና በደም ፍላት፣ጠረጴዛ እዬደበደበ ኦርቶዶክስ የምትሉት ሃይማኖት በራሽያና በኢትዮጵያ ብቻ ያለና ያረጀ፣ያፈጀ፣የአማራው

ሃይማኖት ነው።ካስፈለገ እኔ ጠፍጥፌ እንደምፈልገው አደርገዋለሁ ብሏቸው እንደነበረ ሾልኮ የወጣው ያረጋግጣል።በዚህ አይነት አስተሳሰብና ጥላቻ ከተዘፈቀ ሰው እውነት ይኖራል ብሎ መጠበቅ ጅልነት ነው።ሽማግሌዎቹ ሽመልስ አብዲሳንና የሳሪዎስን ቡድንም አነጋግረው በሽመልስ በኩል ያገኙት ከአብይ የባሰ ስድብና ቁጣ እንዲሁም ከፈለኩኝ ሁሉንም ግልብጥብጡን አወጣዋለሁ የሚል ዛቻ ነበር።በተመሳሳይም የሳሪዎስ ቡድን ከጀመርነው ጉዞ የሚያቆመን የለም ፤ይልቁንስ ሕጋዊ ነኝ የሚለውን ቡድን እጁን እንዲሰጥ ምከሩት የሚል ትእቢት የተመላበት ምላሽ ነበር። ይህንን በሆዱ ይዞ ሕጋዊ ሲኖዶሱን ቀርቡ ለሰላም እጃቸውን እንዲዘረጉ በመማጸን በአብይ የሴራ ሰንሰለት ወይም ወጥመድ እንዲገቡ አድርገዋቸዋል።እንደ እውነቱ ከሆነ ሲኖዶሱ የአብይን ጸባይና ተንኮል እንዲሁም ክህደት ለመረዳት የሚያስችላቸው ብዙ አመላካቾች ነበሩ።ግን ከተቆፈረላቸው ጉድጓድ ውስጥ ለመግባት ,ቃደኞች ሆነዋል።

በመጀመሪያ ላይ ለመነጋገር ያስቀመጧቸው ቅድመ ሁኔታዎች ማለትም  ሕገወጡ ሲኖዶስ በመንግሥት በኩል የተሰጠው እውቅናና ድጋፍ እንዲነሳ፣ከያዛቸው ይዞታዎች እንዲለቅና ቤተክርስቲያኖችና አስተዳደራቸው ከንዋዬ ቅዱሳቱ ጋር ለህጋዊ አካሉ እንዲመለስ፣በህይወትና በንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ እንዲከፈል፣ወንጀል የፈጸሙት ለፍርድ እንዲቀርቡ፣የታሠሩት እንዲፈቱ፣ማሳደድና ማፈኑ እንዲቆም...ወዘተ የሚሉ ነበሩ።ከነዚህ ውስጥ አንዳቸውም ምላሽ ማግኘታቸው ሳይታወቅ ተንደርድሮ ለውይይት ቤተመንግሥት መሄድ የአቋም ጽናት አለመኖሩን ያሳያል።

አብይ አህመድ ፍጹም ትሁትና፣አክባሪና ለሰላሳ ሆኖ እግራቸው ላይ ወድቆ በመቀበሉ ወኔያቸውን ያፈሰሰው ይመስለናል።ያላስታወሱት ቢኖር ክርስቶስንም አሳልፎ የሰጠው በመሳም ፍቅሩን የገለጠለት ይሁዳ እንደነበር ነው። ይህንን የማጭበርበር ገጽታውን የሚሸፍነው አጋሩ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ባስተላለፈው መልእክቱ "በዛሬው ቀን ክርስቶስን በገሃድ በአይኔ አዩሁት"ሲል አብይን ዳግማዊ ክርስቶስ አድርጎ አቅርቦታል።ክርስቶስ የሃዋርያትን እግር የማጠቡን ትህትና በአብይ አህመድ የአባቶችን ጉልበት ከመሳሙ ጋር ያመሳሰለበት ድፍረቱ ነው።

እንደሚሰማው ከሆነማ ሕጋዊ ሲኖዶሱ በፊት ለፊት በር ሲወጡ ፣ ሕገወጦቹም በቤቤተመንሥት በስከጀርባ  በር ገብተው ስብሰባ ማድረጋቸው  ይነገራል።በያዙት መንገድ እንደሚቀጥሉም ይፋ አድርገዋል።ያንን የሚያጠናክርም በሽመልስ አብዲሳ በኩል የኦሮሞ ክልል መግለጫ አውጥቷል። ባወጣው መግለጫም  እርምጃ ከመውሰድ እንደማይቆጠብና በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ ያነጣጠረ ቁሞ ቀሮች የሚል የስድብ ናዳ አውርዷል።ይህ አድራጎቱ ከአብይ አህመድ እውቅና ውጭ ነው አንልም።

ሽመልስ አብዲሳ ቁሞ ቀር ሲል የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን ጽናት፤የማይለወጥ ቀኖናና ፣ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው የማይለወጥ ፍቅር በቋሚነት መኖሩን፣የነበር ያለና የሚኖር መሆኑን እንጂ ከጊዜው የዘመኑ ዕውቀት ጋር  ጋር ያልተገናዘበ ለማለት ነው አንልም።ፈጣሪም ቋሚ ነው፣የነበር ፣ያለና የሚኖር፤ በሽመልስ አብዲሳ በኩል ፈጣሪም ቁሞቀር ነው ማለት ነው።የረሳው ነገር በቁሞ ቀርና በኋላቀር መካከል ያለውን ልዩነት አለማወቁ ነው።እሱ የሚመራበት የፖለቲካ መስመር ከዘመኑ ጋር የማይጣጣም፣የሰው ልጅ ሳይሰለጥን በነበረበት የዋሻ ኑሮ ሲከተል የነበረው ያውሬ ጸባይነትን የሚያንጸባርቅ፣ጨካኝ፣ኢሰብአዊ የሆነ በመሆኑ ኋላ ቀር ተብሎ ይመደባል። የሰውን ልጅ በጎሳ ሸንሽኖ መግደልና ማጋደል፣ጽንስ ሳይቀር ከማህጸን ዘንጥሎ መጣል ከምን አይነቱ የዘመኑ ገጽታ ጋር ይያያዛል?ለዚያም ነው የነአብይና ሽመልስ አነጋዊ እምነትና ፖለቲካኋላቀር የሚባለው።

ሌላው ከአባቶቹ የማይጠበቀው አብይ አህመድ በቀደደው ቦይ ውስጥ ገብተው የተንቦጫረቁበት አባባላቸው ነው። አብይ አህመድ የሕዝበ ክርስቲያኑን ተቃውሞ የፖለቲካ ጥቅም ያላቸው፣መንግሥትን

ለመገልበጥ ሽፋን ያደረጉት ተቃውሞ ነው ሲል መክሰሱን ሁሉም ያውቀዋል።ያንንም ተከትሎ ሊያጠቃ ያሰባቸው እንደሚኖሩም ፍንጭ ወጥቷል።በማሰርም ላይ ተሰማርቷል።ይህንን አባባሉን አባቶችም ተቀብለው ከቤተክርስቲያኗ ጀርባ የፖለቲካ ፍላጎት ያላቸው  ካሉ ከእኛ ጋር አይደሉም፣እናወግዛለን ብለዋል።በዚህ በጎቻቸውን ለአራጅ አሳልፈው የሰጡ መሆናቸውን ልናስታውሳቸው እንወዳለን።

ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ ማንኛውም የማህበረሰብ ጥያቄ ከፖለቲካ የተነጠለ አለመሆኑን ነው። ሃይማኖትም የፖለቲካ መስመር መሆኑን በአረብና በአንዳንድ የሙስሊም አገሮች ያሉትን ሃይማኖታዊ መንግሥታት፣በአውሮፓም በተለይም ፕሮቴስታንቱና ካቶሊኩ ደም አፋሳሽ ጦርነት አድርገው በሥልጣን ቅርምት አገራትን እንደሚያስተዳድሩ የአዬርላንድን ምሳሌ ማድረግ በቂ ነው።ይህንን ስንል የኢትዮጵያም መንግሥታዊ ስርዓት ሃይማኖታዊ ይሁን ማለታችን አይደለም።ፖለቲካ በአዬር ላይ የተንጠለጠለ ሰይጣናዊ መንፈስ ሳይሆን የሕብረተሰብን ጥያቄ፣ሙብትና ጥቅም የሚያንጸባርቅና ምላሽም የሚሰጥ ሳይንስ ነው።አምባ ገነኖች ከሥልጣናቸው ላለመውረድ ግን የፖለቲካን መልክና ትርጉሙን እያጣመሙ  ሕዝቡን ለማሳሳት ይሞክራሉ።አብይ አህመድ የፖለቲካ ሥልጣኑን ጨብጦ የሚፈጽመ ሁሉ ፖለቲካዊ ነው።ለዚያም መልስ ለመስጠት የሚደረገው ትግል የፖለቲካ ትግል ነው። የጳጳሳቱም ትግል ያንን የአብይ አህመድን የፖለቲካ አድማና ሴራ ለመበጠስ እስከሆነ ድረስ ተወደደም ተጠላም ፖለቲካዊ እድምታ አለው።በአገራችንም ሆነ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ የተደረገውና የሚደረገው ዘመቻ ስርአታዊ ነው፣ሥርዓቱ እስካለ ድረስ ፈተናው አይቆምም።የሚቆመው ሥርዓቱ ተወግዶ በአገር ወዳድና ፍጹም  ኢትዮጵያዊ በሆነ ሥርዓት ሲተካ ብቻ ነው።የፖለቲካ ትግሉ የቤተክህነቷን፣የሌሎቹንም የእምነት ተቋማትና ምእመናን ጭምር ነጻ የሚያወጣ ነው።የአገርን አንድነትና ሰላም የሚያረጋግጥ ትግል ነው።አገርና ሕዝብ ሳይኖር የእምነት ተቋማት ሊኖሩ አይችሉም።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በሲኖዶሱ ስለጠፋው በግ መመለስ የሰጡትም አስተያዬት ቀደም ብሎ ያወጡትን ቀኖናዊ አቋም የዘነጋ፣ በይቅርታ ስም ወንጀለኞቹን ለመቀበል የተንደረደሩበት ሊሆን ይችላል የሚል ስጋት አለን።ይህንን ቀና መንፈስ አብይ አህመድና የኦሮሙማው ክንፍ ሊጠቀምበት ስለሚችል ከተመሳሳይ ድርጊት መቆጠብ አለባቸው እንላለን።

የሲኖዶሱን ጥሪ ተከትሎ ለእሁድ የካቲት 5 ቀን 2015 ዓም በአገር ውስጥና በውጭ አገር ሊደረግ የታሰበው ሰላማዊ ሰልፍም ላልተወሰነ ጊዜ መተላለፉን ይፋ አድርገዋል። በአውሮፓ በአንዳንድ ከተማዎችም ሊደረግ ታቅዶ የነበረው ሰልፍ እንዲሁ በይደር ተይዟል።በዋናነት የሚቀርበው ምክንያት ለጥያቄዎቹ አጥጋቢ መልስ ተገኝቶ ሳይሆን ሊከተል የሚችለውን አደጋና የህይወት መጥፋት ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነ እንረዳለን።የአብይ አህመድ መንግሥት ከኦሮሚያ ክልሉ በገፍ ሲያስገባ የከረመው የታጠቀ የአካግ ሠራዊት ጳጳሳቱን በክብር አጅቦ ለመሄድ ሳይሆን ለሰልፍ የሚወጣውን ሕዝብ ለመጨፍጨፍ ነው።አሁንም ቢሆን ይህ የታጠቀ ሃይል ወደ መጣበት አልተመለሰም፣የነሽመልስ አብዲሳም ፉከራ ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው።

የሲኖዶሱን ጭንቀትና ስጋት እንጋራለን።እንደ መንፈሳዊ አባትነታቸው ሰላምን ይሰብካሉ እንጂ ጦርነት አያውጁም።ግን ምእመናኑን ቀስቅሰውና ህይወቱን የገበረበትን ቁም ነገር ዘንግተው ከአብይ አህመድ የሴራ ወጥመድ ውስጥ እንዳይገቡ ያደረብንን ስጋት ለመደበቅ አንሻም።በታሪክም ክርስቲያኖች መከራና ግፍ ሲደርስባቸው አውሮፓውያን  ከድንበራቸው አልፈው የመስቀል ጦርነት ማካሄዳቸውን ሰምተናል።እስላሞቹም እምነታቸው ሲነካ በጅሃድ ጦርነት ይዘምታሉ።በማንኛውም እምነት የሚደረግ ጦርነት የተቀደሰ ጦርነት(Holy War) ነው ይሉታል።ታዲያ የኢትዮጵያ ኦርቶዳክሳውያን ሊያጠፉቸው የመጣውን ለመከላከል ቢነሱ ጥፋትና ወንጀል ሊሆንባቸው፣እንደሃጢያትም ሊቆጠርባቸው አይገባም።

በዚያ ዓይን የምንመለከት ከሆነ በአድዋ ጦር ሜዳ ላይ የዘመተውን የቅዱስ ጊዮርጊስን ጽላትና ቀሳውስት ትክክል አልነበሩም ማለት ነው።

ይህንን ስንል በሰላም መንገድ የሚገኘውን ውጤት በጦር ሜዳ ብቻ ካልተገኘ ማለታችን አይደለም።ግን የኦሮሙማውን ዓላማ ተገንዝበን  ተገቢውን ለማድረግ ማሰብና መዘጋጀት እንደሚገባ ለመጠቆም ነው።ያልጠረጠረ ተመነጠረ! እምብዛም ደግነት ለበግም አልበጃት፣ አስራ ሁለት ሆና አንድ ተኩላ ፈጃት የሚለውን  ማሰቡ ብልህነት ነው።

አብይ አህመድ ሌላ የማጭበርበሪያ መንገድ ሊቀይስ እንደሚችል አውቆ መጠንቀቅና ከዚህ በኋላ ለመደራደር ለቀረቡት ጥያቄዎች ሁሉ ሳይሸራረፉ ተገቢ መልስ ማግኘት፣ማሰርና ማሳደዱ እንዲቆምና ከተማዋን የወረረው የኦሮሙማ ወታደር ለቆ እንዲወጣ መደረግ አለበት።ቆፍጠን ማለት ያስፈልጋል።

ወደ ገሃዱ ዓለም ስንመለስ የኦሮሙማው ቡድን ወደ አዲስ አበባ የሚመጡትን መንገደኞች ከደሴ ሸኖ ላይ፣ከጎጃም በኩል ፍኖተሰላም ላይ  በማገድ በችግር ላይ እንዲወድቁ አድርጓል። ከሲኖዶስ ጋር ስምምነት ማድረጉ ከሕዝብ ጆሮ ሳይደርስና  እነሱም ከመንበራቸው ላይ ሳይቀመጡ በከተማዋ ውስጥ የማሰሩንና የማፈኑን እርምጃ አፋፍሞ ቀጥሎበታል።በአጠቃላይ ሲታይ የኦሮሙማው ቡድን ለጊዜ መግዣ ያደረገw ሽወዳ እንጂ ለዘላቂ ሰላም የሚያበቃ ስምምነት አላደረገም።ሲኖዶሱም ያቀረበው ጥያቄ መልስ እንዳላገኘ በግልጽ ተናግሮ ህዝቡን ለቀሰቀሱበት ትግል እንዲሰለፍ ጥሪ ማድረግ አለባቸው።አለባብሰው ቢያርሱ ባረም ይመለሱ ነውና ለተጨማሪ ጉዳት እራስን ማጋለጥ ተገቢ አይደለም።ሕዝብ ሳይሰለፍና ሳይቃወም  እዬሞተ ነው።በወለጋ፣በሌሎቹም ቦታዎች የሚጨፈጨፈው ሕዝብ እንጂ የጓሮ ሙጃ ወይም አረም አይደለም። ለዚያ መቆም የግድ የፖለቲካና የእምነት መስመርን አይጠይቅም ሰው መሆን ብቻ ይበቃል።

የሞቱትን ነፍስ ይማር ፣ለቤተሰቦቻቸው መጽናናትን ይስጥልን፣ለቆሰሉትም ፈጣን ፈውስን እንመኛለን

ኢትዮጵያ በልጆቿ ተፍራና ተከብራ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!!

የጎሰኞች ስርዓት ይደምሰስ! ሕዝባዊና አገር ወዳድ መንግሥት ይመስረት!!